## ፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹ የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፶፯ /፳፻፲ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪ <u>ማሻሻያ</u>

የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፱/፳፻፰ (በአዋጅ ቁጥር ፶፯ /፳፻፲ እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተተክቷል።

"፲የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ።

፪ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል "ሀ" ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ፊደል "ሀ" ተተክቷል።

"ሀ. የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ።

፫ የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፩ ተተክቷል።

## 1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as "The definition of powers and duties and Re-establishment of the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration (Amendment) proclamation No. 57/2017."

## 2. <u>Amendment</u>

The definition of the powers and duties of the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration proclamation No.49/2016 (as amended by proclamation no.57/2017) is further amended as follows:

1. Sub-Article (10) of article 6 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article(10);

"10. Small and medium manufacturing industry development Agency.

2. Paragraph (a) of sub- article (2) of article 7 of the proclamation is repealed and replaced by the following new paragraph (a).

"a. small and medium manufacturing industry development agency.

3. Article 21 of the proclamation is repealed and replaced by the following new article 21

"፳፩. **የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በንግድ ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ተግባራዊም እንዲሆኑ ያስተባብራል ፣ በበላይነት ይመራል፤

፪ በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሰረት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ሃሳብ ያመነጫል ፣ እንዲጠና እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፫ የአስተዳደሩ ምርት ውጤቶች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚተዋወቁበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊም እንዲሆን ያደርጋል፤

፬ የአስተዳደሩ የንግድ፣ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ባህልና ቱሪዝም፣ የከተማ ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መረጃዎች ተደራጅተው እንዲያዙ ያደርጋል፤

፭ ከአጠቃላይ አዋጆች በመነሳት የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትምንት ፣ ባህልና ቱሪዝም ፣ የከተማ ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደንቦችና መመሪዎችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ለሚመለከታቸው በሥራ ላይ እንዲያውሉት ያስተላልፋል፤

፮ በስሩ የሚመራቸውን ተቋማት አቅም ይገነባል፤

"21 . **Powers and dutiesof Trade, Industry and Investment Bureau.**

The Bureau shall have the following powers and duties;

1. Design a strategy for the implementation of existing policies and strategies on trade. Industry and investment sector coordinate, direct and follow up its implementation;
2. propose investment project ideas that could be realized with investment policy and laws; cause the stady and operation of the same;
3. design strategies to promote the products of the administration with in the country and abroad; cause the implementation of the same;
4. cause to keep information pertinent to the administration trade, industry. Investment, culture, tourism, urban food security and employment creation, technical and vocational educations;
5. prepare regulations and directives on trade, industry. investment, culture and tourism, urban job creation and food security and on technical vocational education and training based on the general proclamations;
6. build the capacity of institutions which are under its supervisions;

፯. በአስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚጠናከሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አስመልክቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል አስተዳደር አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፰. የባህልና ቱሪዝም ልማትን ለማፋጠን የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ፣ ይደግፋል፤

፱. የአነስተኛ መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፈፃሚዎችንና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲቀረጽ ያደርጋል፣ በድጋፍ ማዕቀፎች መሰረት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ውጤታማ ድጋፍ እንዲሰጥ በማድረግ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤

፲. የአስተዳደሩን አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት የሚደግፉ ተቋማትን አቅም በመገንባት የዘርፉን ፈጣን ልማትና ቀጣይነት ያረጋግጣል፤

፲፩. በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩና ለሚሰሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነታቸውን የሚያረጋግጥ የተሟላ እና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

7. design strategies to strengthen the technical and vocational training institution, follow up the implementation enacted policies on technical education and training at of national level, design a strategy at the administrative level, and implement upon approval;

8. design a mechanism to implement policies and strategies enacted to promote culture and tourism development, follow up its implementation; support the same;

9. design supportive formwork by coordinating stake holders implementing organs of the small and medixum manufacturing industry sector; based on the supportive formwork, ensure the implementation of effective support for manufacturing industry;

10. ensure rapid development and sustainability through building the capacity of the administrationals small and medium manufacturing industries development supporting institution;

11. give fulfledged and integrated support to ensure the productiveness of small and medium manufacturing industries engaged in the manufacturing sector;

፲፪ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግመስራት ለማይችሉ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት እየቻሉ ስራ ለሌላቸው እና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍትኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

፲፫ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉትን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሠረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

፲፬.የኢንቨስትምንት ጉዳዮችን በተመለከተ በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያበረታታል፣ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፤ የኢንቨስትምንት አማራጮችን በማስጠናት ያስተዋውቃል፡፤ ኢንቨስትመንት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፭.ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሁብቶች ፣ በመንግስታዊ አካላትና ልዩ ልዩ ባለድርሻዎች መካከል ቅንጅት እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፲፮.ማንኛውም ኢንቨስትመንት ነክ መረጃ ያሰባስባል፤ ያደራጃል ለተጠቃሚውና ውሳኔ ሰጪው አካል ያሰራጫል፤

12. based on urban employment creation and food security strategy, provide development safty net support for those unable to engaged in employment activites or those who are able bodies but unemployed for different resons and for those catagorised below poverty; line there by cause their food security and approve their livelihood on sustainale bases;

13. support and facilitate supportive institution for micro enterprises and small enterprises do not fall under the manufacturing sector so as to make them competent, sustainable, and pave strong ground for the industries development; coordinale the same;

14. encourage, support and promote investment activities being the center of service for investment affairs; cause the study of investment opportunity and promote the same; facilitate the situation to expand investment;

15. create integration and coordinate among investors, public bodies and other steak holders to expand investment; cause to solve bolttenecks in collaboration with relevant public bodies;

16. collect, organize, and disseminate all relevant investment information for users and decision maker;

፲፯.የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስጠናት ያስተዋውቃል፤ ኢንቨስትመንት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፰.በተሰጠው የስልጣን ክልል መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ አፈ ፃፀም ይከታተላል ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፱በስሩ ያሉትን ጽህፈት ቤቶችና ኤጀንሲዎች ያስተባብራል ፣ያቀናጃል፣ ይመራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፳ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፬. የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) ንዑስ አንቀጽ (፲፮) ሆኖአል፤

፭. የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፪ ተተክቷል፤

”፳፪.<u>የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ የአስተዳደሩን የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

17. study and promote investment opportunity facilitate situations to expand investment;
18. issue, authenticale and cancel investment license under its jurisdiction; ensure the proper implementation of conditions included in the investment license and ensure encouragements are used counsistent with the intended objectives;
19. coordinate ,intergrate and lead offices and agencies under its supervision; reander the desired supports;
20. undertate other related activities necessary to achive its objective.

4. Sub-article (11) of article 21 of the preclamation is re-numbered as sub-article (16)
5. Article 22 of the proclamation is repealed and replaced by the following new article 22.

“<u>22. Powers and duties of urban job creation and food security agency.</u>

The Agency Shall have the following pawers and duties;

1. prepare the administration development plan in accordance with the urban employment creation and food security strategy, implement up on approval;

2. የከተሞች የስራ ዕደል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን በሚመለከት የፖሊሲ ጥናቶችን ፣ እና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፣ ለከተማው ህብረተሰብ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ የኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3. በፌደራል ደረጃ የከተሞችን የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስራዎችን ለማስፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲለሙ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ልማት መሰረት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

4. ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት እንዲሁም የከተማ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ደንቦችን፣ መመሪያዎችና እስታንዳርዶችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል ፤

5. የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና የከተማ ምግብ ዋስትና ስትራቴጅዎች በተገቢው ሁኔታ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣ በስትራቴጂዎቹ አፈፃፀም ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

2. Study and submit policy idea and strategic plans pertinent to urban employment creation and food security, facililate studies on the identification of barriers to ensure food security, enterprises development and compectitiveness pertinent to the urban community: implement up on approval;

3. in accordance with the federal policies and strategies promulgated to promote the development of urban employment creation and food security, cause the expansion and development of the micro enterpeises and small scale enterprise do not fall under the manufacturing sector in the urban area; there by so as to serve as a basies for indvstrial development;

4. prepare regulation, directive and standards, which enable to expand and rendering supports service to the micro enterprises and small scale enterprises do not fall under the manufacturing sector as well as enable to ensure food security initiatives; followup its implementation up on approval;

5. ensure the proper implementaion of strategies pertinent to micro enterprises and small scale interprises development do not fall under the manufacturing sector and urban food security; provid quick response for problems arised from the implementation of strategies;

6. በከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

7. የከተማ ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ እንዲገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8. በከተማው የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የሰራ ዕድል ለመፍጠር የስራ አጦች፣መስራት የሚችሉና የማይችሉ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል ፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

9. በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል ፣ ተግባራዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፲. የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ምርቱን ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡ ስለ ተቋማቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖረው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ትምህርታዊ መግለጫዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6. design and implement productive urban safety net program;

7. establish linkage with governmental and civil society organization and facilitate the attainment of financial and material supports so as to ensure the urban food security initiative;

8. collect, organize, analyze and disseminate study based information on unemployed, able body and non-able bady citizens so as to ensure Urban Food Security and Employment Creation;

9. cause the study of micro enterprise and smale scale enterprise do not fall under the manufacturing sector projects in the city that enables the popular participation of unemployed urban youth and women to be productive citizen; follow up the implementation and the same results;

10. facilitate the situation for the product of the sector to get domestic and export market access; in cooperation with concerned organ design different strategies which enable to promote the product and to publicize the product and to publicize the institutions among to the residence; cause the preparation of educational descriptions, coordinate the execution, and follow up the same;

፲፩ በከተማው ህብረተሰብ ውስጥ የሚታየውን የተዛባ የስራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ ግንዛቤ ማዳበሪያና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ያከናውናል፤

፲፪ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማደራጀት፣ ለማጠናከር እና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል የተሻሻሉ አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከሉን አቅም ይገነባል ፣ ማዕከላቱን ያስተባብራል፤

፲፫ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል ፣የድጋፎች ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

፲፬ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያደራጃል ፣ ይመራል ፣ ያስተባብራል ፤ የስልጠና እና የብድር አገልግሎት ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስርና ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭ ሞዴል ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይፈጥራል፣ ያሸጋግራል፤

፲፮ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

11. carryout awareness creation and public mobilization to reverse the distorted attitude of employment behavior among the urban residents;
12. build the capacity of the centers through establishing improved invoative systems so as to organize and strengethen the one stop service and render the same properly; coordinate the centers;
13. collect and organize information required for the development of micro enterprises and small scale enterprises do not fall under the manufacturing sector, distribute to the users; conduct study on the demand and supply of supports;
14. organize, lead, coordinate micro enterprises and small scale enterprises do not fall under the manufacturing sector; facilitate training, credit service, technology and production equipment supplies; and provide supports for marketing linkages;
15. establish model micro enterprises and small scale enterprises do not fall under the manufacturing sector promote the same;
16. render auditing and inspection service for the micro enterprises and small scale enterprises do not fall under manufacturing sector;

፲፯ በከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናትና በመቀመር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ያስፋፋል፤

፲፰ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፮.የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፫ ተተክቷል፤

"፳፫.<u>የአነስተኛእና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

????? ?? ????? ????? ???? ??????

፩ የኢንዱስትሪ ልማት ዘርፉ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አባላትን ባከተተ መልኩ የስትሪንግ ኮሚቴ በማዋቀር በአስተዳደሩ ከፍተኛ አመራር እንዲመራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፤የአሰራር መመሪያዎችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፪ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎችን ይቀርፃል፣ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫ ሀገራዊ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ እቅዶችን፣ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ በመንግስት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፣

17. study, synthesized and scale up the best practice achieved on urban employment creation and food security interventions through different means;

18. performed relevant activities necessary for the fulfillment of its objectives.

6. Article 23 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Article 23.

``23. **<u>Powers and duties of small and medium manufacturing industry development Agency</u>.**

The agency shall have the following powers and duties;

1. establishing industry development sector steering committee with member of relevant bodies and facilitate to be lead by higher administration leaders; cause the design and implementation of working directives.
2. prepare a frame work for support which enables to accelarate of small and medium manufacturing industry development; and implement same upon approval;
3. based on national industry development policies and strategies, formulate policies, strategies, plans, programs and projects that supports the acceleration of small and medium manufacturing industry development; and implement same up on approval by the government;

፬ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይሠራል፣ ለተወዳዳሪነታቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፭ በአስተዳደሩ መዋቅራዊ ፕላን መሰረት ለማኑፋክቸሪን ኢንዱስትሪ ልማት የተለየ መሬት ይረከባል፣መሰረተ ልማት እንዲሟላ ያደርጋል፣ በካቤኔ ውሳኔ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት እና በተለዩ የግል አምራች ባለሀብቶች እንዲተላለፉ ያደርጋል፤አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ያስተዳደራል፤

፮ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለመደገፍና ለማስተባበር ኤጀንሲው ስር የተደራጁ ተቋማትን እንዲሁም የቀበሌ ተቋማትን የማስፈፀም አቅም ይገነባል፣

፯ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የእሴት ሰንሰለት መሠረት በማድረግ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በፍላጎትና በዕድገት ደረጃ ላይ የተመሠረተ የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን እንዲያቀርቡ እንዲሁም በኤጀንሲው ስር በሚደራጀው ተቋም አማካይነት የኢሬክሽንና ኮሚሽኒግ ስራዎችን ድጋፍ ያደርጋል፤

4. undertake activities that creat conductive environment for the development of small and medium manufacturing industry, identify constrains that affect their competitiveness through studies, and provide remedy for same;
5. handover the delinated land for industrial development based on the administrative structural plan; cause the development of infrastructure; cause the transfer of the same for manufacturing industry cluster development and identified private manufacturing investors based on the cabine decision; follow up the implementation; administer the same;
6. support and coordinate small and medium manufacturing industry development; in addition to this beside this build implementation capacity of kebele institution;
7. based on the value chain, integrate and facilitate the supportive institution to give training, supply finance and technological input on their need and growth of small and medium manufacturing industry;

፰ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ለይቶ ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ያሰራጫል፣

፱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁ ያደርጋል፣

፲ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ጠቃሚ የሆኑ የአዋጭነት ጥናቶችና ፕሮጀክት ፕሮፋይሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነተናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

፲፩ .ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለማጠናከር እና ለመፍጠር የኢንተርፐረነርሺፕ ፕሮግራም በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የኢንዱስትሪያል ኤክስቴንሽን አገልግሎት በቅንጅት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በተገቢው እንዲሰጥ በማድረግ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ድጋፍ ያድረጋል፤

8. conduct local as well international bench marking studies and identify formulate, and disseminate best practices that facilitate the development and competitiveness of small and medium manufacturing industry;

9. provide necessary support for the establishment of sect oral associations of small and medium scale manufacturing industry;

10. cause undertaking of feasibility studies important for the development of small and medium manufacturing industries and sector, prepare project profits, collect, analyze, organize and disseminate information for the beneficiaries;

11. design and implement entrepreneurship programs in order to strengthen industrialists and create new one support the provisions of extension services. in desired a coordinated manner for small and medium manufacturing industries, there by increase production and prouctivity;

፲፪ .በአስተዳደሩ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት በማደራጀት መሠረተ ልማት የተሟላላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች እና የእርስ በእርስ የገበያ እድል ሊፈጥር የሚችል ዘመናዊና አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የመሸጫና ማሳያ ማእከል እንዲገነቡ ተገቢውን እገዛና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፫.ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ይደግፋል፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እርስ በእርስና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት በአቅርቦትና በምርት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጥሩ ያደርጋል፣ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፣

፲፬.ከጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ወደ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ተግባራዊ ያደርጋል፣

12. provide, by way of organizing clusters of small and medium manufacturing industry necessary, support and provide capacity building assistance to administration in order to develop industry zones and commercial centers that have all the requisite inform structure;
13. Support the transformation of small manufacturing industry to medium manufacturing industries and from medium manufacturing industry to large scale manufacturing industry; create development linkage for small and medium manufacturing industries with that of the large scale industry in terms of inputs, supply production and technology support to make the industry beneficiaries of local and foreign market linkages;
14. establish mechanisms for the transformation of micro manufacturing industry to small manufacturing industry and implement same in co-ordination with appropriate bodies;

፲፭.የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነትን ለማሳደግ፣ እንዲሁም የሚያመርቷቸው ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከጥናትና ምርምር ተቋማት፣ ከዘርፉ ልማት ኢንስቲትዩቶች፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ ከካፒታል ዕቃዎች አከራይ ኩባንያዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሰው ሀብት ልማት፣ በጥናት፣ ምርምርና ሥርፀት ምርት ልማትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በቅንጅት ይሠራል፣ ቁርኙቱን ያጠናክራል፣ ያስተባብራል፤

፲፮.አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ተወዳዳሪ ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ፣ የእውቅና እና ሽልማት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤

፲፯. ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን አውደ-ርዕይ፣ አውደ ጥናት ሰሚናሮችና ተመሳሳይ መድረኮችን በማዘጋጀትና በማስተባበር በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተመረቱ ምርቶችና ቴክኖሎጂዎች እንዲተዋወቁና ኢንዱስትሪዎች የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉና በውድድር መንፈስ አቅማቸውን እያሳደጉ እንዲሄዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤

15. work in collaboration with universities, research institutions, sectoral development institutes, technical and vocational education and training institutes, capital goods leasing companies and other stakeholders in the areas of human resource development, research and studies, technology transfer, and infrastructure development to improve the productivity. Standards and quality of products as well as competitiveness of small and medium manufacturing industry, and strengthen the linkage; coordinate the same;
16. establish a system based on appropriate study for provision of incentive, recognition and award to small and medium manufacturing industry to assure competitiveness; and ensure implementation of same;
17. in cooperation with other concerned bodies, support and facilitates the promotion of products and technologies of small and medium manufacturing industry as well as facilitate experience sharing among industries by arranging and coordination exhibition, symposia, seminars and other similar forums in coordination with different bodies;

፲፰.እንደአስፈላጊነቱ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን በቅርንጫፍ ደረጃ ያቋቁማል፣ እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፱.የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የምርት ደረጃ ስልጠና እንዲሰጣቸው በማድረግ የጥራት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬሽን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

፳.የአነስተኛና መካከለኛ ማኒፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ጥራት ያለው ምርት ማምረት እንዲችሉ ለመደገፍ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥና በወጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ያደርጋል፤

፳፩.በኢንዱስትሪ መንደር የሚገነቡ የኢንዱስትሪ ኘሮጀክቶች የኢንዱስትሪ ፖሊሲና ስትራቴጂ ህጎችና መመሪያዎችን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ በኢንዱስትሪ መንደር ከሚገቡ ባለሃብቶች ጋር ውል ይፈጽማል፣ በውል መሰረት መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፳፪.የማምረቻ ኢንዱስትሪው በብቃት ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችሉ የማምረቻ መሳሪያና መሸጫ ማዕከላት የሚገቡ አካላትን በግልፅ ተለይቶ በተዘጋጀው መስፈርት ተመልምለው እንዲገቡ ያደርጋል፤

18. establish center rendering one-stop-shop service for small and medium manufacturing industry accordingily; and provide support for establishment of the same;

19. support the provision of quality assurance for small and medium manufacturing industry through offering them production standared training;

20. make co-operate with domestic and foreign private and public institutions with similar objectives to support small and medium manufacturing industry in order to provide services that meet international standards;

21. cause the construction of the industries project carried out in the industry village consistent to the industry development policy and strategy laws and directive. may enter agreement with investors that enter in the industry village; follow up and supervise the contract implementation; control the same;

22. identify and enter the manufacturing industries in the manufacturing and market center based on the clearly identified criteria to make more competent the manufacturing industry;

፳፫.የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የወጡ ህጎችን መሰረት በማድረግ በፕሮጀክት ደረጃ እና በማምረት ሂደት የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

፳፬.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤

፳፭.የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንድስትሪ ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ተቋማትን ሊያራጅ ይችላል ፤ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፯.ከአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፭),(፲፮),(፲፯),(፲፰),እና (፲፱) ተጨምረዋል፤

‹‹፲፭.የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ እምነቶች እንዲሁም የብዙሃንና የሙያ ማህበራትን ምዝገባ ያካሂዳል፣ ፍቃድ ይሰጣል፤

‹‹፲፮.የሃይማኖት እና የእምነት የጋራ ጉባዔ እንዲጠናከር ያደርጋል፣ በሃይማኖት እና በእምነት ተቋማት መካከል በውስጣቸው ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ አሠራር እንዲሰፍን በማድረግ የሰላም እሴት ግንባታ ተልዕኳቸውን መወጣት እንዲችሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

23. support and work with relevant bodies to accomplish the manufacturing industries with environmental laws that related to the project level and production process;

24. own property, enter into contract, sue and sued in its own name;

25. Perform other related activities necessary for the attainment of its objectives.

7. the following new sub- Article (15),(16),(17) (18) and (19) are adeded under sub-Article (14) of Article 31 of the proclamation;

``15. register and give license to religious institution as well as faith, civic and professional association;

``16.strength religious and belief congregation; induce democratic system within religious and faith institution to surmount the building of peace values mission;

‹‹፲፯.ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በፀረ-አክራሪነትና ጽንፈኝነት የትግል ስልቶች ላይ ሥልጠና በመስጠት ግንዛቤያቸውን ያሳድጋል፤

‹‹፲፰.ሃይማኖት ነክ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በየደረጃው በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የሃይማኖት ተቋማት ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አክብረው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

‹‹፲፱.የብዙሃንና የሙያ ማህበራት ነፃነታቸው እንደጠበቁ በሀገር ዕድገት፣ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግና ከመንግስት ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፍ አስመልክቶ አስፈላጊውን ምችችት ያደርጋል፡፡

፲፭.አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፲፭), (፲፮), (፲፯), (፲፰), (፲፱), (፳), (፳፩), (፳፪),(፳፫),(፳፬),(፳፭),(፳፮),(፳፯),(፳፰),(፳፱),(፴),(፴፩),(፴፪),(፴፫),(፴፬),(፴፭),(፴፮), እና(፴፯), እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፳), (፳፩), (፳፪), (፳፫), (፳፬), (፳፭), (፳፮), (፳፯), (፳፰), (፳፱), (፴), (፴፩), (፴፪), (፴፫), (፴፬), (፴፭), (፴፮), (፴፯),(፴፰),(፴፱),(፵),(፵፩),እና (፵፪) ሆነዋል፡፡

``17. give training and raise awareness of different segment of society on strategy of anti fundamentalist (bigoted) Struggle;

``18. facilitate to resolve the good governance question by different level of relevant bodies; Support and follow up the religious institution to operate based on the constitution;

``19.facilitate the civic and professional association to contribute to the growth of the country, peace and building of democratic system;

15. sub- Article (15), (16), (17), (18), (19), (20), (21), (22), (23), (24), (25), (26), (27), (28), (29), (30), (31), (32), (33), (34), (35), (36) and of (37) Article 31 of the proclamation are re-numbered as sub – Article (20), (21), ), (22), (23), (24), (25), (26), (27), (28), (29), (30), (31), (32), (33), (34), (35), (36), (37), ) (38), (39), (40), (41), and (42), respectively.

፰. ከአዋጁ አንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፲፯) ቀጥሎ የሚከተሉትን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) (፲፱)እና (፳) ተጨምሯል፣

"፲፰.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማ የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተላልፏል፡፡

"፲፱. ኢንዱስትሪን የሚመለከቱ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ልማት ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ ተላልፏል፡፡

"፳. ኢንቨስትመንት የሚመለከቱ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ልማት ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ተላልፏአል፡፡

፫.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ጥቅምት ፳፫ቀን ፳፻፲ ዓ.ም**

**ኢብራሂም ዑስማን**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

8. The following new sub- Article (18),(19), and (20) are aded under sub-Article (17) of Article 63 of the proclamation:

18. The rights and obligations given to micro and small scale enterprise development Agency are hereby transferred to urban job creation and food security Agency.

19. The rights and obligations given to the industry and investment development office related to industry are hereby transferred to small and medium manufacturing industry development agency.

`` 20. The rights and obligations given to the industry and investment development office related to investment are hereby transferred to the trade industry and investment bureau.

**3. <u>Effective date</u>**

This proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dir Dawa this 2ed day of,**

**November 2017**

**Ibrahim Osman**

**Mayor of Dire Dawa Administration**